# ባዮፕሲ

አንዳንድ ምልክቶች ወይም የበሽታ ምልክቶች ካልዎት፣ ወይም ሐኪምዎ አንድን የሚያሰጋ አካባቢ ለይቶ ካወቀ፣ ሐኪምዎ ባዮፕሲ እንዲያደርጉ ሊያዝልዎ ይችል ይሆናል።

ባዮፕሲ ማለት፣ ከሰውነትዎ ክፍል ላይ ትንሽ የስጋ ቁራጭ ወይም የሴል ናሙና የመውሰጃ ያሰራር ሂደት ነው።.



እንደ የቅልጥም መቅኔ እብጠት፣ የሰውናት አካል ወይም ቆዳ የመሳሰሉ የሰውነት የአካል ክፍሎችን በባዮፕሲ ሊመረመሩ ይችላሉ።

ከሰውነትዎ ክፍል ለምርመራ የተወሰደበት ቦታ ጉዳት አይደርስበትም።

ለምርመራ የሚወሰደው ትንሽ ቁራጭ ስለሆነ ሰውነትዎ ተሎ ይድናል።



ናሙናው ወደ ላቦራቶሪ ተወስዶ፣ ካንሰር ወይም ሌሎች ችግሮች እንዳይኖሩ በማይክሮስኮፕ ይመረመራል።

ባዮፕሲን ተጠቅሞ አንድ አጠራጣሪ የሰውነት ክፍል ካንሰር መሆኑንና አለመሆኑን በእርግጥ ለማወቅ ያስችላል።

ሌሎች ችግሮች እንዳሉ ለማወቅ ደግሞ ባዮፕሲን መጠቀም ይቻላል።እነዚህም ኢንፌክሽንና ያልተጠበከ እብጠትን ነው።



ባዮፕሲን በተለያዩ መንገዶች ማድረግ ይቻላል። አንዳንድ የፓዮፕሲ አይነቶች ቀዶ ጥገናን ማድረግ ያስፈልገዋል።

ሌሎች ዓይነቶች ደግሞ መርፌን ብቻ ተጠቅሞ ትንሽ ስጋ ማንሳት ብቻ ይሆናል።

ጥቂት ባዮፕሲዎች ሀኪሙ ቢሮ ውስጥ ሊደረጉ ይችላሉ። ሌሎቹም ሆስፒታል ውስጥ ይደረጉ ይሆናል።

እርስዎ የሚያደርጉትን የባዮፕሲ ዓይነት ሐኪምዎ ይገልጽልዎታል። የማይገባዎት ነገር ካልዎ ጥያቄ ይጠይቁ።



ልክ እንደ ሌሎች ያሰራር ሂደቶች፣ ባዮፕሲን ማድረግ የራሱ የሆነ ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችንና ያልተፈለጉ ውጤቶችን ሊያስከትል ይችላል። ሐኪምዎ ከባዮፕሲ ጋር በተዛመደ ሊገጥሙ ስለሚችሉ ደህንነቶችና ችግሮችን ይገልጽልዎታል።

ለባዮፕሲ ቀጠሮ ሲመጡ ጓደኛ ወይም ቤተሰብ አብሮ ቢሆን ይቀላል።አንዳንድ ባዮፕሲ ማደንዘዣ መሰጠት የሚያስፈልጋቸው  ይሆናል ስለዚህ ሰው ይዘው እንዲመጡ ይጠየቃሉ።

የባዮፕሲ ያሰራር ሂደት የሚመረመረውን የአካል ክፍል ባካባቢው ካሉት የአካል ክፍሎች ይለያል። ይህም ጤነኛ ያልሆኑት ሴሎች ጤነኛ ከሆኑት ሴሎች ጋር እንዳይነካኩ ይከላከላል። ባዮፕሲ ካንሰርን ሊያሰራጭም፡ የካንሰር ሴሎች እንዲስፋፉ ወይም እንዲያድጉም አያደርግም።

የሚያደርጉትን የባዮፕሲ ሁኔታ ታይቶ፣ ምንም ዓይነት መዘጋጀት እንዲያደርጉ ላይጠየቁ ይችሉ ይሆናሉ።

በሌላ ወገን ደግሞ፣ ከምርመራው በፊት ምንም ምግብ እንዳይበሉ፣ ከምርመራው በኋላ ወደ ቤት የሚያደርስዎትን ሰው እንዲያዘጋጁ፣ ወይም በየጊዜው የሚወስዷቸውን መድሃኒቶችን ያወሳሰድ መንገድ እንዲቀይሩ፣ ወዘተ ሊጠየቁ ይችሉ ይሆናሉ።

በባዮፕሲው ወቅት ህመም ማስታገሻ መድሃኒት ይሰጥዎታል። ይህም ባካባቢው ላይ ብቻ የሚሰራ ማደንዘዣ (በባዮፕሲው አካባቢ ያለውን ቦታ ለማደንዘዝ የሚወጋ መርፌ) ሊሆን ይችላል። ወይም፣ የህመም ማስታገሻ ወይም ማፍዘዣ (ሰውነትዎን ዘና ለማድረግ) መድሃኒትን መስጫ የአይ ቪ ምስመር ሊደረግልዎ ይችል ይሆናል።

ሐኪምዎ የባዮፕሲውን ቦታ በትክክል ለማወቅ እንዲረዳው ራጂ፣ ሲቲ ስካን ወይም አልትራ ሳውንድ ይደረግልዎት ይሆናል።



ከምርመራው በኋላ፣ ባዮፕሲ በተደረገበት ቦታ ላይ ስንብራት፣ አለመመቻቸት ወይም እብጠት ሊታይ ይችል ይሆናል።ይህ ችግር ለብዙ ግዜ አይቆይም። ከባዮፕሲው በኋላ እራስዎን እንዴት መንከባከብ እንደሚችሉ ሓኪምዎ ይገልጽልዎታል፣ አስፈላጊም ከሆነ የህመም ማስታገሻ መድሃኒት ያዝልዎታል።



የባዮፕሲ ናሙናዎች ለመጠናት ግዜ ይወስዳሉ። የባዮፕሲ ውጤትዎን ላማግኘት ምን ያህል ግዜ እንደሚወስድ ሐኪምዎ ይገልጽልዎታል።

የባዮፕሲ ውጤቶች የህክምና አሰጣጡን አቅጣጫ በመቀየስ ላይ ይረዳሉ። ለምሳሌ፣ ካንሰር መኖሩ ከታወቀ፣ የባዮፕሲ ውጤቱ ምን ዓይነት እንደሆነ በትክክል ያሳያል። ይህም እርስዎና ሐኪምዎ በመተባበር፣ ለእርስዎ የተሻለውን የሕክምና እቅድ ለማዘጋጀት ይረዳል። ወይም፣ ባዮፕሲ አንድ የተወሰነ ዓይነት ኢንፌክሽን እንዳለ ለይቶ በማሳየቱ፣ ሐኪምዎ የበለጠውን መድሐኒት እንዲመርጥ ይረዳዋል።

ባዮፕሲዎን አስመልክቶ ያሆነ ጥያቄ ካልዎት ሐኪምዎን ወይም ነርስዎን ይጠይቁ።

**A project by Health Roads Media and EthnoMed**
This project has been funded in whole or in part with Federal funds from the Department of Health and Human Services, National Institutes of Health, National Library of Medicine, under Contract No. HHS-N-276-2011-0008-C with the University of Washington. Thank you to Safeway Foundation for its support to Harborview Medical Center's EthnoMed for the development of cancer-related content.